*በሎስ አንጀለስ የቅንጅት የርዳታና ልማት ድርጅት*
*Kinijit's Los Angeles Support and Development*
*Association for Democracy (KINIJIT)*
*5768 W. Pico Blvd., Suite No. 207, LA, CA 90019*
*E-mail: kinijitla@kinijit.org Website www.kinijitla.org*

# ይድረስ ለመሪዎቻችን፡

በብዙሃን ኢትዮጵያውያን ድምጽ መመረጣችሁ እንደጥፋት ተቆጥሮ ከሃያ አንድ ወራት በላይ በወያኔ እስር ቤት ስትማቅቁ የነበራችሁ መሪዎቻችን ዛሬ ተፈታችሁ ከምትወዱዋቸው ቤተሰቦቻችሁ ለመገናኘት ስለበቃችሁ እጅግ በጣም ደስ ብሎናል። ክቡራን መሪዎቻችን የኢትዮጵያንና የልጆችዋን ፀሎት የሚሰማ አምላክ እንኳን ወደ እየቤተሰቦቻችሁ ለመቀላቀል አበቃችሁ።

ለኢትዮጵያ ህዝብ መስዋዕትነት በመክፈል፣ ፊትለፊት በቆራጥነት በመጋፈጥ፣ በአገራችን የሚካሄደውን ዋነኛ የሰብዓዊ መብት ረገጣ እና የፍትህ ጉድለት ለዓለም በማገለጣችሁ የኢትዮጵያ ህዝብ ውለታችሁን በልዩ ታሪክ ይመዘግበዋል።

እኛ የሎስ አንጀለስ ነዋሪ የሆን ኢትዮጵያውያኖችም የደስታችሁ ተካፋይ መሆናችንን በሙሉ ልብ ልናረጋግጥላችሁ እንፈልጋለን።

በውጭ አገርም ሆነ በአገር ቤት የሚገኙ ወገኖች ለእናንተ መፈታት ሲጸልዩ የነበር ከመሆኑም በላይ የወያኔ ኢህአዴግን አስከፊ ሥርአትና፣ የፍርድ አልቦ መንግሥት ለማስተካከልና በኢትዮጵያ ላይ የተጫነው ስርዓት የለሽ አስተዳደር ስር እንዳይሰድ የተቻላቸውን ከማድረግ አልተቆጠቡም። በርካታ ኢትዮጵያውያን በያሉበት አገር ድምጻቸውን በማሰማት፣ መንግስቶቻቸውን በመማጸን፣ የህዝብ ድጋፍን በመጠየቅ የኢትዮጵያዊነት ግዴታቸውን ሲወጡ ቆይተዋል። የቅንጅትን ዓላማ እውን ለማድረግ ከቅንጅት ጎን በጠንካራ አቋም በመቆም የታገሉ ጊዜያቸውንና ገንዘባቸውን ያበረከቱ ጥቂቶች አይደሉም። የቅንጅት መንፈስ እኛ ኢትዮጵያውያን በይበልጥ እንድንቀራረብና፣ ብሎም ትግላችንን በተደራጀ ሁኔታ እንድንቀጥል በማድረጉ መስዋእትነታችሁ በከንቱ ላለመሆኑ ዋቢ ይሆናል እንላለን።

## ውድ መሪዎቻችን፡

እናንተ ባስተጋባችሁት የቅንጅት መንፈስ የኢትዮጵያ ህዝብ መብቱን ለማስጠበቅ ቆርጦ የተነሳ በመሆኑ ኩራት ሊሰማችሁ ይገባል። የዓለም ህዝብ ማንነታችሁን ያውቃል። አምነስቲ ኢንተርናሽናል የህሊና እስረኞች መሆናችሁን ለዓለም መንግስታት ሲያስታውቅ ቆይተዋል። ታላላቅ መንግሥታት ያለአግባብ መታሰራችሁን ሲያወግዙ ቆይተዋል።

ይህ ጠንካራ የህይወት ክፍያ የተደረገበት የቅንጅት እንቅስቃሴ በእናንተ አመራር የታለመለትን ግብ እንደሚመታ ጥርጥር የለንም። ጠንካራ ትብብር፣ ተሳትፎ እና ንቃት እንደሚያስፈልገን ተገንዝበናል። በዚህም ግንዛቤ የሚጠበቅብንን በማድረግ አብረናችሁ እንደምንጓዝ ቃል እንገባለን።

በሎስ አንጀለስ የቅንጅት ድጋፍ እና ልማት ድርጅት ለዲሞክራሲ
www.kinijitla.org